# ለአፍሪካ የማይናወጥ አቋምና ጽናት

ከብርሃኑ ተሰማ(ኢዜአ)

ጊዜው 1975 ነበር። ሊቢያ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት(አአድ) 19ኛውን የመሪዎች ጉባዔ ለማስተናገድ ሽር ጉድ ብትልም፤ ኃያል አገር አሜሪካ በመሪዋ በፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬገን አማካይነት ጉባዔው እንዳይሳካ ጥረት በማድረጓ ውድቅ እየሆነ ተደጋጋሚ ችግር ይፈጠራል።

ከአንዴም ሁለቴ በአሸባሪነት በተፈረጀችው አገር እንዳይካሄድ የተፈረደበት ጉባዔ መጨረሻ ላይ ደርሶ ወደ ትውልድ አገሩ ይሂድና ጉባዔው እንዲካሄድ ተወሰነ። በወቅቱ የሊቢያ ዓረብ ጀማሂሪያ አብዮት መሪ ኮሎኔል ሙአማር ጋዳፊ በአሜሪካው መሪ "እብድ ውሻ" እየተባሉ ይጠሩ ስለነበር ጉባዔውን እንዳይካሄድ ሲያሰነካክሉት ቆይተዋል።

የቅርቡ የሊቢያ አብዮትና በአብዮቱ የተበሉት ጋዳፊንም ማስታወስ ይቻላል።ከ42 ዓመታት የእሳቸውና የቤተሰቦቻቸው አገዛዝ በኋላ አምና የሆነውን ሁላችንም እናስታውሳለን ብዬ አስባለሁ። ወደ 30ዓመታት ትውስታዬ ልመለስና አአድን የወለደችው አዲስ አበባ በአስቸኳይ መሪዎቿን ጠርታ ለማስተናገድ በቃችና የአገሪቱ መሪ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የዓመቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀመንበር ሆነው ተመረጡ።

ታዲያ በወቅቱ ከፖለቲካው ፍትጊያና እሰጥ አገባ በላይ ዛሬም ከህሊናዬ የማይጠፋው የናይጄሪያው ፕሬዚዳንት ሼሁ ሻጋሪለኢትዮጵያ ሬዲዮ የተናገሩት ነበር።" ድርጅቱ ወደተወለደበት አገር ሲመጣ ከሕመሙ ተፈወሰ" ያሉት።

ኢትዮጵያ ባለፉት 50 ዓመታት ውስጥ ድርጅቱን በማዋለድ፣በማሳደግም ወደ ኅብረትነት እንዲቀየር በማድረግም ታሪካዊ ድርሻዋን ስትወጣ ኖራለች።

በአገሪቱ የትኛውም የፖለቲካ ሥርዓት ይሁን የቱም በአፍሪካዋ ወንድማማችነትና እህትማማችነት መንፈስ ተቀብሎ በማስተናገድ፣ ጭቆናና በደልን፣ ግፍና ብዝበዛን በመቃወም አቅሟ የፈቀደውን ሁሉ አድርጋለች። ግጭቶች ሲከሰቱ በማብረድም ተሳትፎዋ ቀላል አልነበረም።

በአህጉሪቱ የሚፈጠር አለመጋጋትን በመረጋጋት በመተካት የተጎዱትን በማቋቋም የተቸገሩትን በመርዳት የማይናወጥ አቋሟን ስታንጸባርቅ ኖራለች።

ኢትየጵያ አህጉሪቱን ከቅኝ አገዛዝ ሙሉ በሙሉ በማውጣትና አፍሪካውያን ነጻነታቸውንና ክብራቸውን ለመመለስ እንዲሁም አፍሪካን ወደ ኢኮኖሚ ዕድገት ለመምራት በተደረገው ትግል የማይነጥፍ አስተዋጽኦ ስታደርግም ቆይታለች።

ከድርጅቱ ምስረታ በፊት አፍሪካን ከሁለት ከፍሏት በነበረው የካዛብላንካና የሞንሮቪያ ቡድኖች መካከል የነበረው የአካሄድና የአስተሳሰብና ልዩነት እንዲፈታ በማድረግ ታላቅ አስተዋጽኦ አበርክታለች።

ኢትዮጵያን ወራሪውን የጣልያን ኃይል ታግላ ነጻነቷን በማስመለስ ያስመዘገበችው ድል በአህጉሪቱ ለነጻነት ሲደረግ የነበረውን ትግል በማቀጣጠል በርካታ አገሮች ነጻነታቸውን እንዲጎናጸፉ አድርጓል።

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1960ዎቹ አፍሪካውያን በቅኝ አገዛዝ ሲሰቃዩ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት በሕግ ትሟገትላቸውና ትከራከራላቸው  የነበረችም አገራችን ናት።
በቅኝ አገዛዝና በአፓርታይድ ሥርዓት ሲሰቃዩ የነበሩ አፍሪካውያን የሞራል፣የዲፕሎማሲና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ ሚናዋን ተወጥታለች።በተለይም ለደቡብ አፍሪካ፣ ለናሚቢያና ለዚምባብዌ የነጻነት ትግል ወታደራዊ ስልጠና በመስጠት ያደረገችው አስተዋጽኦ በታሪክ ሲወሳ ይኖራል።

የአሁኗ የኮንጎ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ(ዲ አር ሲ)በያኔዋ ቤልጂዬም ኮንጎ የነበረውን ችግር ለመፍታት የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ኃይል  እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1960-64 በነበረው ጊዜ ግዳጁን ሥነ ምግባር በተሞላበት በተሳካ ሥራ አከናውኗል።

በሩዋንዳ  እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1990ዎቹ በተከሰተውና የዓለም ሕዝብ ባስደነገጠው የዘር መፍጀት እንቅስቃሴ ሰላም እንዲያስከብሩ ከተደረጉት አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ነበረች።በዚህ የአንድ አገር ሕዝቦች እርስ በዘር ተለያይተው እንዳይተላለቁ ለማድረግ ባደረገችው ተሳትፎ ለወገን ኩራት የሆነ ተግባርም ታላቁን መሪ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የአገሪቱን ከፍተኛ ኒሻን አሸልሟቸዋል።

ላይቤሪያ ባለፈው የአውሮፓውያን አሥርት መጨረሻ ላይ ከፍተኛ የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ነበረች።አገሪቱን ወደ ሰላምና መረጋጋት ጎዳና ለመመለስ በተደረገው ሂደት የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ኃይል ተሳትፎ ወደር አልነበረውም።ሰላምና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን በማድረግም ሚናውን  ተጫውቷል።

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር አዲሱ ሚሌኒየም ሲጀመር ቡሩንዲ  ሁቱና ቱሲ የተባሉ ጎሳዎቿ  ግጭት ውስጥ ነበሩ።ዘር ለይቶ የተፈጠረውን ግጭት ለማስቆም በአፋጣኝ ሰላም አስከባሪ ኃይላቸውን እንዲልኩ ከተደረጉት አገሮች መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ነበረች።በዚህም ታሪካዊ አስተዋጽኦዋን አበርክታለች።

በሱዳን ዳርፉር ግዛት ከሌሎች አገሮች ጋር በመሆን ባሰማራችው ሰላም አስከባሪ ሠራዊት የእርስ በርስ ግጭት  እንዳይከሰት በማድረግ ላይ መሆኗም ይታወቃል።

ሱዳንና ደቡብ ሱዳን በይገባኛል በሚከራከሩበት የአቢዬ ክልል ከዓለም ብቻውን የተሰማራ ሰላም አስከባሪ ኃይልበተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥላ ሥር በማሰማራት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነቷን ያሳደገ ተግባር እያከናወነች ነው።በሁለቱም አገሮች መንግሥታትና ሕዝቦች ያላት አክብሮትም ከፍተኛ ሆኖ ይታያል።

አገራችን በምሥራቅ አፍሪካ አገሮች ሰላም፣ጸጥታና መረጋጋት ከፍተኛ ሚና እየተጫወተች ባለችው ሚና በሶማሊያ የነበረውን መንግሥት አልባነትና አክራሪነት በመታገልም ውጤታማ መሆኗንም ማስተዋል ተገቢ ይመስላል። ሰላሙ የተረጋገጠ፣በኢኮኖሚ የበለጸገና ዴሞክራሲ ያበባቸው ጎረቤቶች የጋራ ጥቅም መሠረት ናቸው በማመንም በመሥራት ላይ ትገኛለች።

ባለፉት ግማሽ ክፍለ ዘመን በሞሮኮና በአልጄሪያ መካከል ፣ናይጄሪያ ውስጥ የቢያፍራ የመገንጠል እንቅስቃሴና በሱዳን የኛኛ እንቅስቃሴ ከማዕከላዊ መንግሥታት ጋር የነበራቸው ግጭት በመፍታት ታሪካዊ አስተዋጽኦ አበርክታለች።

ኢትዮጵያ በኢኮኖሚው መስክ ያላት አህጉራዊ ትብብር በምሥራቅና ማዕከላዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ(ኮሜሳ)የተጠናከረ ውህደት ለመፍጠር ያላት ሚና ከፍተኛ ነው።

በመሠረተ ልማት ግንባታ መስክ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለመሳብም ጥረት ታደርጋለች። ወጣቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግም በመሥራት ላይ ነች።
ከጅቡቲ፣ሱዳንና ደቡብ ሱዳን ጋር የመንገድ ግንኙነት በመፍጠር ለጋራ ጥቅም በመትጋት ላይ ትገኛለች።ከጅቡቲ ጋር የሚያገናኝ የባቡር መሥመር ግንባታው በመካሄድ ላይ ሲሆን፣ከኬንያ ጋር የሚያገናኘው መሥመር በቅርቡ ይጀመራል ተብሎ ይጠበቃል።

ለጅቡቲ የኤሌክትሪክ ኃይል በማቅረብ ላይ ተጠቃሚ ከማድረጓን በላይ፣ ኬንያን በተመሳሳይ ሁኔታ ተጠቃሚ እንድትሆን እንቅስቃሴ እያደረገች መሆኗን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጃዎች ያመለክታሉ።

የናይል(የአባይ)ን ውሃ አጠቃቀም ፍትሃዊ በሆነ መልኩ መጠቀም አስፈላጊነቱ አምና እየሰራች ነው።የናይል ተፋሰስ አገሮች የጋራ ማዕቀፍም ፊርማ ወደ ማጽደቅ ሂደት በመግባት ላይ ነች።ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በመገንባት 6ሺህ ሜጋ ዋት በማመንጨት ዓላማዋ ከአገር ውስጥ ፍጆታ አልፎ ጎረቤት አገሮችንም መጥቀም ነውና።

ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ልማት አዲስ አጋርነት(ኔፓድ)የገባችውን ቃል ለማክበሯ ከላይ የተጠቀሱት ፕሮጀክቶች ሁነኛ ማስረጃዎቿ ናቸው።

በአህጉረቱ መልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲን ለማስፈን የተያዘውን ጥረትም በአፍሪካ እርስ በርስ መገማገሚያ ስልትም እየተተገበረችው መሆኑንም ማወቅ ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት ሕንጻ የተገነባበትን 2ሺህ ስኩየር ሜትር መሬት መስጠቷ በታሪክ ተመዝግቧል።

ባለፈው ዓመት የተመረቀው አዲሱ የአፍሪካ ኅብረት ጽህፈት ቤት ግንባታ መሬት በነጻ በመስጠትና የቻይና መንግሥት በማግባባት ያደረገችው አስተዋጽኦ ቀላል የሚባል አይደለም። በአዲስ አበባ ኤምባሲያቸውን ለከፈቱ የአፍሪካ አገሮች ሕንጻ ግንባታም ቦታ በመስጠትም ድጋፏን ሰጥታለች።

አገሪቱ የአአድ/አኅ ጽህፈት ቤትን በአዲስ አበባ ከተማ በማስተናገዷ በሁሉን በፊት በኢትዮጵያና በሌሎች የአፍሪካ አገሮች መካከል ያለው ግንኙነት ተሻሽሏል።

በሁለተኛ ደረጃ ከተማዋ የዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲ መናኸሪያ ለመሆን በቅታለች።በዚህ ረገድ የሚወዳደሯት ኒው ዮርክ፣ጄኔቭና ብራስልስን የመሰሉ ከተሞች ብቻ ናቸው። በከተማዋ የሚደረጉት ጉባዔዎች፣ስብሰባዎችና ዐውደ ጥናቶችና ሌሎችም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በማስገኘትም ያስገኙት ዋጋ ከፍ ብሎ ይታያል።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን ወልዳ፣አሳድጋና ወደ አፍሪካ ኅብረትነት ያደረሰችው አገር የተዋሃደችና አንድነቷ የተጠበቀ አፍሪካን በመገንባት የአፍጉሪቱ ሕዝቦች በእኩልነትና በጋራ እንዲኖርባት ትፈልጋለች።

ለግማሽ ክፍለ ዘመን የዘለቀው አፍሪካን የማስተናገድና የአህጉሪቱ መዲና ሆኖ መገኘት ታላቅ ኩራት ነው።ኩራቱም በኢትዮጵያዊነታችን የሚያስከብርንና የሚያስወድደን መሆኑም አያከራክርም።

አገራችን አህጉሪቱን በሁለንተናዊ መልኩ አርአያ ሆና ለመምራት የሚያስችላት አቅም አዳብራለች።ማንም ይሁን የትም ኢትዮጵያ የአፍሪካ ክብርና ኩራት መሆኗን ከሚመሰክክርበት ደረጃ አድርሶናል ማለትም ይቻላል።

**ኢትዮጵያ የአፍሪካን አንድነትና ኅብረት ወደላቀ ደረጃ በማድረስ ድርሻዋን መወጣቷን ትቀጥልበታለች!!!**